# ተንበርክከን ከምንኖር ቆመን ብንሞት ይሻላል!!

ፍራንክሊን ደ.ሩዝቬልት

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ሊቀመንበር በኢትዮጵያ ለፖለቲካ ፓርቲ መሪነት የበቃችው የመጀመሪያዋ ወጣት ሴት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የፈፀመችው ተግባር በርዕስነት የተጠቀምኩበትን ዘመናት ያስቆጠረ አባባል እንዳስታውስ አደረገኝ፡፡

የተባለችውን ፈፅማ ሥጋዊ ሕይወቷን እያስደሰተች በመንፈስ ተንበርክካ መኖርን አልፈቀደችም፡፡ በቃሏ ፀንታ፣ እምነቷን ጠብቃ፣ የሞራል የበላይነትን አሳይታ ወደ እስር ቤት ወረደች፡- አንበርክከው ሊያኖሯት የሞራል የበላይነቷን ሊነጥቋት ብዙ ያሰቡ፣ ብዙም የሠሩ ወገኖችን አሸነፈቻቸው፡፡ ሽንፈታቸው የፈጠረባቸው ስሜት ደግሞ ለበለጠ ጥፋት፣ ለበለጠ የህግ ጥሰት ዳረጋቸውና ህገ-መንግሥቱን ረግጠው በእስር ቤት ሰዎች እንዳይጐበኟት ከለከሉ፡፡ አልገባቸው እንደሁ እንጂ በዚህም ተሸንፈዋል፡፡. . .

ሄገል «በሰንሰለት ታስረህ ነፃነት ሊሰማህ ይችላል፡፡» እንዳለው ወ/ት ብርቱካን እስር ቤት በጨለማ ቤትም ተጥላ፣ ጠያቂም ተከልክላ ነፃነት እንደሚሰማት በቅርብ የሚያውቋት ይበልጡንም ከሰሞንኛው ተግባሯ በሚገባ የተረዷት ሁሉ የሚመሰክሩት ነው፡፡ በሷ ላይ የሆነውንና የሚሆነውን ሁሉ የፈፀሙና እየፈፀሙ ያሉት ግን በምንም ሁኔታ ነፃነት ሊሰማቸው አይችልም፡፡

የላይኞቹ ጭንቀት፣ የሥልጣን ጉዳይ፣ ጥላቻና በቀል እየገፋፋቸው የሚፈፅሙት ሲሆን በየደረጃው ወደታች ያሉት ደግሞ ለመኖር ለእንጀራ ሲሉ በትዕዛዝ የሚሠሩት ነው፡፡

ወ/ት ብርቱካንን ለማንበርከክ ከእስር በፊት ብዙ ነገሮች ተከናውነዋል፡፡ የእሷ የእምነት ጥንካሬ እየጨመረ ለማንበርከክ የተነሱትም እልህቸው እየበረታ ፍፁም ህገ-ወጥ በሆነ ሁኔታ እስሩ ተፈፅሟል፡፡ ህገ-ወጥ ያልኩት የህግ ባለሙያ ሆኜ አይደለም፡፡ ከይቅርታ አዋጁ ጋር እየተጣቀሰ የሚነሳውን ጉዳይ ለተከታተለ በተለይ የፍትህ ሚኒስቴር ታኅሣሥ 20 እና 21 ቀን 2001 ዓ.ም. በተከታታይ ባወጣቸው መግለጫዎች የጠቀሳቸው አንቀጾች የተለያዩ መሆናቸውን በጥሞና ላስተዋለ የድርጊቱን አፈፃፀም ህገ-ወጥ ብሎ ለመፈረጅ የህግ አውቀት አያስፈልገውም፡፡ ይህን የህግ ባለሙያዎች የበለጠ ቢተነትኑት ይሻላል፤ የሙያ ግዴታም አለባቸውና፡፡

## <u>ወ/ት ብርቱካን በአውሮፓ</u>

በቅንጅት አንድ ሆኖ በአመራሮች መታሠርም ይበልጥ አንድነቱን አጠናክሮ የነበረው በአውሮፓ የተለያዩ ሀገራት የሚገኘው ኢትዮጵያዊ አመራሮቹ ከእስር ከተፈቱ በኋላ የፈጠሩት መከፋፈል አከፋፍሎት ከፊሉንም ተስፋ አስቆርጦት በዚሁ ምክንያት በአውሮፓ የሚታየው የኢትዮጵያኖች እንቅስቃሴ የተዳከመ ሆኖ ነበረ፡፡ ይህ ደግሞ በመንግሥት በኩል በጣም የሚፈለግ መሆኑ የሚያነጋግር አይደለም፡፡

የወ/ት ብርቱካን የአውሮፓ ጉዞ በዚህ የተዳከመ እንቅስቃሴ ላይ የመነቃቃት ስሜት የፈጠረና ወደ ቀድሞ አንድነታቸው የሚመለሱበትን፣ ወደ እዚህ መምጣት የማይችሉትም በልዩነታቸው ተከባብረው በሀገር ጉዳይ የጋራ የሆነ ሥራ መሥራት የሚችሉበትን መንገድ ያመላከተ ነበር ማለት

ይቻላል፡፡ በአውሮፓና አሜሪካ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ተጠናክረው ሀገራዊውን ትግል ለማገዝ በሚያስችል መልኩ መሰለፍ ከቻሉ የሚያደርሱበትን ጫና የሚያውቀው መንግሥት የአንድነት ፓርቲ በሊቀመንበሩ አማካኝነት የፈፀመውን ተግባር በዝምታ የሚያየው ሊሆን ያለመቻሉ የሚጠበቅ እንጂ እንግዳ ነገር አይደለም፡፡ ችግሩ የተጠቀመበት መንገድ ላይ ነው የሚንፀባረቀው፡፡

ተቃዋሚው መንግሥትን ለመለወጥ የሚያደርገው ትግል ሕጋዊ ብቻ መሆን እንዳለበት ሁሉ መንግሥትም በተቃዋሚዎች ላለመበለጥ የሚያደርገው ሁሉ ፍፁም ሕጋዊ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ «ሰው ነብርን መግደል ሲፈልግ ስፖርት ይለዋል፡፡ ነብሩ ሊገለው ሲፈልግ ግን አውሬነት ይለዋል፡፡» የሚለው የበርናርድ ሾውን አባባል የሚያስታውስ ድርጊት ይሆናል፡፡

<u>ብርቱካን ወደ ሀገር ቤት አትመለስም</u>

አንድነት ፓርቲ በሁለት የልዑካን ቡድኑ አማካኝነት በአውሮፓ የተለያዩ ሀገራት የፈፀመው የፓርቲውን መሠረት የመትከል ተግባር ያላስደሰታቸው ወገኖች ብርቱካን ወደ ሀገር ቤት አትመለስም የሚል ወሬ በስፋት ረጩ፡፡ ይህ ዝም ብሎ የተወራ ተራ ወሬ ተደርጐ ሊወሰድ አይችልም፡፡ ታቅዶ ታስቦበት በዝግጅት የተፈፀመ በኢትዮጵያ ውስጥ የመፎካከር አቅም ያለው ፓርቲ እንዳይኖር የማድረግ ሥራ ነው፡፡ ወ/ት ብርቱካን የሰጠችው መልስ ደግሞ የድርጊቱ ፈፃሚዎች ሽንፈታቸውን አምነው እንዲቀመጡ የሚያደርጋቸው አልሆነም፡፡ ሽንፈትን ለመቀበል ንፁህ አዕምሮ፣ ቅን ልቦና፣ የሞራል የበላይነትና ህገ አክባሪነትን ይጠይቃል፡፡ ይህ የሌለው ወገን ይበልጥ ጥላቻ ያሳድራል፣ ለበለጠ በቀል ይነሳሳል፣ ያሰበውን በምንም ይሁን በምን መንገድ ካልፈፀመ እንቅልፍ እይተኛም፡፡

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ወደ ሀገርሽ አትመለሽም ይባላል? ተባለ ስትጠየቅ በደርግ ዘመን ተመሳሳይ ጥያቄ የተጠየቀ ሰው ሀገሬን ለአስር አለቆች ትቼ አልሸሽም በማለት የሰጠውን መልስ በማስታወስ ነበር ምላሽ የሰጠችው፡፡ ይህ ለኢህአዴጋዊያን ሽንቋጭ መልስ ነው፡፡

<u>መታሠር ይገባታል</u>

ወ/ት ብርቱካን እዛው አውሮፓ እያለች ወደ ሀገር ቤት አትመለስም የሚለውን ምኞታቸውን ተፈፃሚ ለማድረግ የተነሱ ኃይሎች እሷን ማስፈራራት አንዱ ስልታቸው ነበር፡፡ ለዚህም አፍቃሪ መንግሥት ተብለው በሚታወቁ ዌብ ሳይቶች ወ/ት ብርቱካን እንዲህ አለች፡- ይህን ተናገረች መንግሥት ይህን በዝምታ ሊያልፈው አይገባም፡፡ መታሠር አለባት ወዘተ በማለት በስፋት ፃፉ፡፡ በእርግጥ እነዚህ ኃይሎች በመንግሥት ላይ ተፅዕኖ የማሳረፍ አቅም እንዳላቸው አሳይተዋል፡፡

የዚህ ዘመቻ ዓላማ ብርቱካንን ማሣሰር ነው ብሎ ማሰብ የዋህነት ይሆናል፡፡ ምክንያቱም አውሮፓ ላይ ልትታሰር አትችልምና ዓላማና ፍላጐቱ የማሰር ከሆነ ሀገር ቤት እስከምትገባ አድፍጦ መጠበቅ ነበር የሚሆነው፡፡ በዌብ ሳይቶች የተካሄደው ዘመቻ ዓላማ ወ/ት ብርቱካንን በአወሮፓ ማስቀረት ሲሆን ግቡ ደግሞ አንድነትን ማዳከም ነው፡፡ ሊቀመንበሩ የኮበለለበት ፓርቲ እንዴት ተጠናክሮ ሊወጣ ይችላል?

ይህ ዓላማና ፍላጐት ግን በወ/ት ብርቱካን የእምነት ፅናት ከሽፈ፡፡ ሁሉንም የተባለ የታሰበውን ሁሉ ወደ ጐን ብላ ሀገሯ ተመለሰች፡፡

## ህዳር 27 ቀን 2001 ዓ.ም. የአንድነት ሕዝባዊ ስብሰባ

አውሮፓ እንድትቀር ብዙ የተባለባትና የተሠራባት ብርቱካን አዲስ አበባ የገባችው ፓርቲው ሕዝባዊ ስብሰባ ባዘጋጀበት ዋዜማ ነበር፡፡ ግንቦት 7/1997 ዓ.ም. የተጣለው የሕዝባዊ ስብሰባ እገዳ በይፋ ባልተነሳበት ሁኔታ የመጀመሪያ የሆነው የአንድነት የመብራት ኃይል ስብሰባ ውጤት ለመንግሥት ኃይሎች ያልጠበቁት ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ሌላው ሌላውን ሁሉ ትተን ኢህአዴግ ከአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ ጋር ለመታረቅ በሚል ከፍተኛ ባለሥልጣናት በየወረዳው ወርደው ካወያዩ በኋላ ሕዝብንና ተቃዋሚውን አለያይተናል አብዛኛውንም የእኛ ደጋፊና አባል አድርገነዋል ብለው አስበው ነበር፡፡ ነገር ግን እምነታቸው እንደሚየዝያ 29/1997 ሁሉ ትክክል እንዳልሆነ ያሳየ ስብሰባ ነበር፡፡

የአውሮፓው ትኩሳት ያልበረደላቸው ወገኖች የመብራት ኃይሉን የሕዝብ መነሣሣት ሲያዩ ሊፈጥርባቸው የሚችለውን ስሜት መገመት አይከብድም፡፡ እናም «ይህች ባቂላ ካደረች አትቆረጠምም» አሉና በለጋው ለመቅጨት አውጠነጠኑ ስልት ቀየሱ፡፡ . . . ለአራት ቀናት ዕቅዳቸውን ካብላሉ በኋላ ወደ ተግባር ተሸጋገሩ፡፡

ወ/ት ብርቱካን በቃል መልዕክት ወደ ፖሊስ ኮሚሽነሩ ቢሮ ተጠርታ «በውጪ መገናኛ ብዙሀን ይቅርታ አልጠየኩም ብለሻል ይህንን የማታስተባብይ ከሆነ መንግሥት ይቅርታውን ያነሳል» የሚል ምክርም ማስፈራሪያም ቢጤ ተናገራት፡፡ ይቅርታ የመስጠትም ሆነ የማንሳት ሥልጣን በአዋጅ የተሰጠው ለይቅርታ ኮሚሽኑና ለፕሬዝዳንቱ ሆኖ እያለ ፖሊስ ይህን ለማለት የበቃው በየትኛው የህግ ድንጋጌ ነው ብሎ ለሚጠይቅ ሰው መልሱ ቀላል ነው፡፡ አላማው ወ/ት ብርቱካንን ማንበርከክና አንድነትን ማዳከም እንጂ የማሰር ዝግጅት እንዳልነበረ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የተፈፀመው ሂደት ያሳያል፡፡ ከመነሻው ለማሠር የተዘጋጀ አካል ቢያንስ ለማስመሰል እንኳን ህጋዊውን መንገድ ተከትሎ ይጓዝ ነበር፡፡ በተለይ ደግሞ ቀን አነጋግረዋት ማታ በመንግሥት መገናኛ ብዙሀን አብይ ዜና ሆኖ በየሰዓቱ መነገሩን፣ በማግስቱም የአዲሰ ዘመን ዜና ሆኖ መታተሙን ላጤነ ሰው አላማው አስፈራርቶ ማነበርከክ እንደነበረ በሚገባ ይገነዘባል፡፡

ማስፈራራት የሚቻለው የሚፈራ ሲገኝ መሆኑን ኮሚሽነሩ ያወቁ አይመስልም፡፡ ደሞስ ፖሊስ ሕግ ያሰከብራል እንጂ ሰው ያስፈራራል እንዴ?

## ማስጠንቀቂያ ማስፈራራትና ማሸበር

የመጀመሪያ ሙከራቸው ያልሠራላቸው ወገኖች ሁለተኛ ዙር ጠንከር ያለ ሥራ ጀመሩ፡፡ ወ/ት ብርቱካንን እንደመጀመሪያው በፖሊስ የቃል መልዕክት ቢጠሯት ልትሄድላቸው ስላለቻለች ቀንና ቁጥር የሌለው መጥሪያ በያዙ ሁለት ሲቪል ለባሾች ከቢሮዋ ተወሰደች፡፡ የያዙት መጥሪያ ማዕከላዊ ወንጀል ምረመራ ትፈለጊያሽ የሚል ቢሆንም እነርሱ ግን ፖሊስ ኮሚሽን ወሰዷት፡፡ ኮሚሽነሩም የተናገርሽውን እንድታስተባብይ ሦስት ቀን ጊዜ ሰጥተንሻል የሚል አጭር ማስጠንቀቂያ እንደሰጧት ወ/ት ብርቱካን ገልፃለች፡፡ ሌላው አስገራሚ ነገር መጥሪያውን መልሽ መባሏ ነው፡፡ ይህ ለምን እንደተፈለገ ብዙ ግምት መሰጠት ቢቻልም ወ/ት ብርቱካን ግን እንደማትመልስላቸው ገልፀች፡፡ ወደ ማዕከላዊ ወስደው በማስፈራራት ለመንጠቅም ሞከሩ በአቋሟ ፀናች፡፡ ከዚህም አልፈው ግን በኃይል ለመንጠቅ አልደፈሩም፡፡ ፍላጐታቸውን ያለማሳካታቸው ግን አላበሳጫቸውም ማለት አይቻልም፡፡

ወ/ት ብርቱካን በተሰጣት የቀነ ገደብ ውስጥ ተንበርክካ የተባለችውን እንድትፈፅም ለማድረግ በምርጫ 97 ወቅት የቅንጅት መሪዎችን እየተከታተሉ ያሰፈራሩ እንደነበረው፡- የሚከታተሏት መኪናዎች ተመደቡ፡፡ የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ የአሁኖቹን የድርጊት አፈፃፀም ያየበት አጋጣሚ ባየኖርም በ97 እንደተመለከተው ተከታታዮቹ መኪና መግጩት ይከጅላቸዋል፣ መስታወት አውርደው ፀያፍ ስድብ ይሳደባሉ፣ ሽጉጥና ክላሽ በማሳየት ያስፈራራሉ፣ ተከትለው ቡና ቤት ይገባሉ ወዘተ፡፡ ያሁኖቹ ለብርቱካን የተመደቡት ሰዎች ይህን ስለመፈፀማቸው የማውቀው ነገር የለም፡፡

ይህ ሁሉ ግን ብርቱካንን የሚበግራት አልሆነም፡፡ ቃል የእምነት እዳ ነው እንዲሉ የመጨረሻዬ ያለችውና ቃሌ የሚል ርዕስ የሰጠችውን ሃሳቧን ያሰፈረችበትን ፅሑፍ በጋዜጦች አስነበበችን፡፡ የጉዳዮ መነሻና መድረሻ ይቅርታ አልጠየኩም ብለሻል የሚል ብቻ ቢሆን ኖሮ ወ/ት ብርቱካን በዚህ ደብዳቤዋ ግልፅ መልስ የሰጠችበት በመሆኑ ወደ ተከታዮ እርምጃ መሄድ ባላስፈለገ ነበር፡፡ በሀገር ሽማግሌዎች አማካኝነት በቀረበ ሰነድ ላይ መፈረሟን በዚህም የኢትዮጵያን ሕዝብ እና መንግሥት ይቅርታ መጠየቋን ገልፃለች፡፡ በወቅቱ ከሽማግሌዎቹ የተነገረውም የሚያስረዳው ይህንኑ ነው፡፡

<u>እስራት</u>

ወ/ት ብርቱካንን ማንበርከክ እንደማይቻል የተገነዘቡት ኃይሎች በተለይ (ቃሌ) ብላ የፃፈችው ቃሏ ላይ እውነታውን ፍርጥ አድርጋ ማሳየቷ እልህ ውስጥ ያስገባቸው ይመስላ ል፡፡ በዕለተ ቅዳሜ በወጡ ጋዜጦች ላይ ፅሑፉ ተነቦ እሷ የታሰረችው ሰኞ እለት ነው፡፡ ኮሚሽኑ መቼ ተሰብስቦ ወሰነ? ለፕሬዝዳንቱስ መቼ ቀርቦ ተፈረመ? ይህ ሁሉ ጥድፊያስ ለምን አስፈለገ? ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳት ይቻላል፡፡ ሕግ ሲጣስ የኢህአዴግ ሰዎችም ቢሆኑ ነግ በእኔ ብለው ሊጠይቁ ይገባል፡፡ ሰለ ህግ መጣስ፣ ስለ ሥርዓቱ ብልሹነት የገኘው ፓርቲ ሰዎች የሚናገሩት ሀገር ጥለው ባሕር ተሻግረው ሲኮበልሉ ብቻ መሆን የለበትም፡፡

አንዲትን ሴት ልጅ ለመያዝ በአራት መኪና አስር ያህል ታጣቂ ማሰማራትና እንግልት መፈፀም የድርጊቱን ምንነት ቁልጭ አድርጐ የሚያሳይ መስታወት ነው፡፡ አብረዋት የነበሩትን አዛውንቱን ፕ/ር መስፍንን በመምታት (እሳቸው በአሜሪካ ድምፅ ራድዮ እንደገለፁት) ጀግንነቱን ያሳየው ታጣቂ ድርጊትም በሰዎቹ ውስጥ የተፈጠረው የጥላቻ ስሜት የቱን ያህል ሥር የሰደደ መሆኑን ያሳየ ነው፡፡ «ሕጐች በጦር መሣሪያ መሃል ዲዳ ናቸው፡፡» የሚለውን የሲሴሮ አባባል ጠመንጃ ያዦች መስበር ካልቻሉ ነገ ወር ተረኛ ተጠቂ ሊሆኑ እንደሚችሉ ከወዲሁ ማወቅ ብልህነት ነው፡፡

<u>ድርጊቱ የሚፈጥረው ትውስታ</u>

ወ/ት ብርቱካንን ለማንበርከክ የተኬደበትን መንገድ ሳይ ፈጥኖ ወደ አእምሮዬ የመጣው ትውስታ ጠ/ሚኒስትር በነበሩት አቶ ታምራት ላይኔ ላይ የተፈፀመው ድርጊት ነው፡፡ ወደ ወህኒ ከመውረዳቸው በፊት ፓርላማ ቀርበው የተናገሩትና በቀጥታ የቴሌቪዥን ስርጭት የተከታተልነው ትዕይንት ከእስር ቤት ሲወጡም (ላቀባበል ይመስላል) በዋዜማው በቴሌቪዥን ቀርቦ ነበር፡፡ አቶ ታምራት ፓርላማ ቀርበው «ተመክሬ ልመለስ አልቻልኩም፡፡» በማለት የተናገሩት ከእስር አላዳናቸውም፡፡ እንደውም ለሁለት በደል ነው የዳረጋቸው፡፡ ለፕሮፓጋንዳ በትርና ለእስር፡፡ ይታያችሁ እንግዲህ! ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በተፈፀመባት ድርጊት ሁሉ ተንበርክካ የተባለችውን ብትፈፅም ኖሮ ምን ይገጥማት

ነበር? ያሏትን ከፈፀመች በኋላ እንደ አቶ ታምራት ባያስሯት እንኳን ከዛ በኋላ የምትኖረው ተንበርክካ ነው:: ተንበርክኮ እየኖሩ ደግሞ ታማኝ እንጂ ተቃዋሚ ፖለቲከኛ መሆን አይቻልም:: አጃቢ የሚሆን እንጂ ተፎካካሪ የሚሆን ፓርቲ መምራት አይቻልም:: እንደ ፍራንክሊን ዲ. ሩዝቬልት አባባል «ተንበርክኮ ከመኖር ቆሞ መሞት የሚመረጠው» ለዚህ ነው:: ብርቱካን የፈፀመችውም ይህንኑ ነው::

<u>ለመሆኑ ብርቱካን የምታስተባብለው ምን ነበር?</u>

ቀደም ብሎ ከፖሊስ የተነገረው ኋላም በፍትሕ ሚኒስቴር መግለጫ የተጠቀሰው «ይቅርታ አልጠየኩም ብለሻል» የሚል ነው:: ወ/ት ብርቱካንም ይቅርታ አልጠየኩም አላልኩም ነገር ግን ይቅርታ የጠየኩት በሀገሪቱ የይቅርታ ሕግ ሳይሆን በሀገር ሽምግልና ጥረት ነው:: ይህን ክጀም አላውቅ ልክደውም አልችልም ብላለች:: ዋንኛው አደራዳሪ ሽማግሌ ፕ/ር ኤፍሬም ይስሐቅም ታኅሣሥ 17/2001 ዓ.ም. ለንባብ በበቃ አንድ ሣምንታዊ ጋዜጣ ላይ «ወ/ት ብርቱካን በራሳቸውም ሆነ በቤተሰባቸው በተፃፈ ደብዳቤ ይቅርታ አልጠየቁም» በማለት አረጋግጠዋል:: ጉዳዩ በርግጥ ከይቅርታው ጋር ተያይዞ የተነሳ ብቻ ቢሆን ኖሮ እዚህ ጋር ማብቃት ነበረበት:: ሁኔታው የጅብና የአህያዋን ነገር ይመስላል:: አያ ጅቦ ከወራጁ ወንዝ ከላይ ሆኖ እይጠጣ ከበታቹ ያለችውን አህያ አታደፍርሽብኝ እንዳለው ማለት ነው:: ነገሩ የገባት አህይትም «አያ ጅቦ ሳታማካኝ ብላኝ» የሚል ነበር መልሷ::

አዎ! በዚህ ፅሑፍ ከሞላ ጐደል የተጠቀሰውን በወ/ት ብርቱካን ላይ የተፈፀመን ድርጊት ስናጤን የምናገኘው እውነት ጠንካራ ሰላማዊ ትግልና ታጋይ እንዳይኖር የማድረግ ዓላማ ውጤትን ነው:: የይቅርታው ጥያቄ ጉዳይ አታደፍርሽብኝ ያለው የጅቡ ምክንያት ዓይነት ሲሆን የብርቱካን መልስም ሳታመካኝ ብላኝ ነው:: ለዚህም ነው በሰላማዊ ትግሉ መስመር ላይ የተሰለፉ ወገኖች ሁሉ በብርቱካን ላይ የተፈፀመውን ድርጊት በኢትዮጵያ ሰላማዊ ትግል ላይ የተመዘዘ ሰይፍ አድርገው የተመለከቱትና ተቃውሟቸውን ያሰሙት::

ሁሉም እንደ ብርቱካን «ተንበርክኮ ከመኖር ቆሞ መሞትን ቢመርጥ» የኢትዮጵያ ትንሳኤ በአጭር ጊዜ እውን ይሆን ነበር:: ምናልባትም የብርቱካን መታሰር የትንሳኤው ጅማሮ ይሆን?